# የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net

sh1@ttomar.net


ገ_ዐዓ_20150116_ዐማርኛ

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የ2015 ፡ ዓ.ም. ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ መልእክት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡–

## « አንዲት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ ሞት ! »

ለንደን ፥ መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ!**

የዘመናት ፡ ጌታ ፥ ቸር ፡ አምላክ ፡ እንኳን ፡ ከዘመን ፡ እዘመን ፡ በደኅና ፡ አሸጋገረኽ ፡ እያለ ፥ ውጥን ፡ አካልኽ ፥ **የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት** ፡ ( ኢ.ሀ.ሥ.አ. ) ፡ መልካም ፡ ምኞቱን ፡ በፍጹም ፡ ትሕትና ፡ ያቀርብልኻል ።

መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 1945 ፡ ዓ.ም. ፥ አስቀድሞ ፡ ለ60 ፡ ዓመታት ፡ "ኤርትራ" ፡ በሚል ፡ ስም ፥ በቅኝ ፡ ገዢዎች ፡ ቀንበር ፡ ሥር ፡ ወድቀው ፡ የነበሩት ፡ የባሕር ፡ ምድር ፡ እና ፡ የደንከል ፡ ጥንታውያን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፥ በነዋሪዎቻቸው ፡ ትግል ፡ እና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፥ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ውሳኔ ፡ ዳግመኛ ፡ ከእናት ፡ ሀገራቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ በድበላ ፡ ( በfederation ) ፡ ሥርዐት ፡ የተቀላቀሉበት ፡ ዕለት ፡ ነው ። ዘንድሮ ፡ 70ኛ ፡ ዓመቱን ፡ እናስባለን ።

ዳሩ ፡ ግን ፥ **« አንዲት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ ሞት ! »** ፡ በሚል ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ የታገሉ ፡ ነዋሪዎቻቸውም ፡ ኾኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፥ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ያመለከተቱት ፡ ለመዋሐድ ፡ እንጂ ፡ ለመዳበል ፡ አልነበረም ። በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ የተጫነባቸው ፡ ይህ ፡ ደባል ፡ ዐዳር ፡ ለዐሥር ፡ ዓመታት ፡ በገቢር ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፥ ከጥቅሙ ፡ ጕዳቱ ፡ ማመዘኑን ፡ ሲያረጋግጡ ፥ የክፍለ ፡ ሀገሪቱ ፡ ነዋሪዎች ፥ በተወካዮቻቸው ፡ አማካይነት ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ መክረውና ፡ ዘክረው ፥ በሙሉ ፡ ድምፅ ፡ ውሳኔ ፡ ድበላውን ፡ ገፍተው ፥ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ፈጽሞ ፡ የመዋሐድ ፡ ውዴታቸውን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ አስተላለፉ ። የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥትም ፥ ነዋሪዎቹ ፡ ያስተላለፉለትን ፡ ውዴታ ፡ አክብሮ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ክዋኔ ፡ በማሻሻል ፥ ኅዳር ፡ 5 ፡ ቀን ፡ 1955 ፡ ዓ.ም. ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራን ፡ 14ኛ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ አድርጎ ፡ በእግዚአናው ፡ አዋሐዳት ። ዘንድሮ ፥ ኤርትራ ፡ ከእናት ፡ ሀገሯ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የተዋሐደችበትን ፡ 60ኛ ፡ ዓመት ፡ እናስባለን ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

ካ11 ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ ግን ፥ በ1966 ፡ ዓ.ም. ፥ ከሺሕ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡

ራስኸ ፡ በእግዚእናኸ ፡ የከወንከው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊው ፡ መንግሥትኸ ፡ ከውጭ ፡ በተመራ ፡ ዐመፅ ፡ ተደርምሶ ፥ እንሆ ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ለ 49 ፡ ዓመታት ፡ በተፈራረቁብኸ ፡ የውንብድና ፡ አገዛዞች ፡ ሥር ፡ ወድቀኸ ፥ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራም ፡ ዳግም ፡ ተገንጥላ ፥ ሀገር ፡ ኢትዮጵያም ፡ በ"አፓርትሀይድ" ፡ የድበላ ፡ ወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ ተገርኝታ ፥ የመበታተንና ፡ የጥፋት ፡ አደጋዎች ፡ ተደቅነውብኻል ።

**የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት** ፡ ( **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ) ፥ መፍትሔ ፡ ይኾንልኻል ፡ ብሎ ፡ ባመነው ፡ መሠረት ፥ የሥልጡንሕዝብነትኸን ፡ ርትዕ ፡ ተመርኵዞ ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኸን ፡ መልሶ ፡ ለማቋቋምና ፥ በአንድነት ፡ ሥልጣንኸ ፡ አማካይነት ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናኸን ፡ ለማስከበር ፡ ገና ፡ በ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ ትግሉን ፡ ተቀላቅሏል ። የዘመኑ ፡ መርዘም ፡ የትግሉን ፡ አስቸጋሪነት ፣ የባለጋራዎቻችንንም ፡ ኀያልነት ፡ የሚያመለክተውን ፡ ያኽል ፥ ወደ ፡ ፊት ፥ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኸ ፡ ሞልቶ ፡ በሚገኝበት ፡ ሰዓት ፡ ያንኑ ፡ ያኽል ፡ ፍጡን ፡ ፈውስ ፡ እንደምታገኝበት ፡ ያረጋግጣል ። ይህ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኸ ፡ የሚገሠግሥበት ፡ መርሐ ፡ እና ፡ ስልት ፡ አስቀድሞ ፡ በኤርትራ ፡ የአንድነት ፡ ትግል ፡ ዘመን ፡ ( 1933 – 1945 ፡ ዓ.ም. ) ፥ በወቅቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አገናኝ ፡ መኰንን ፡ በነበሩት ፡ በሊ. ፡ **ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ** ፡ አሳሳቢነት ፥ የክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ የመዋሐድ ፡ ትግሉን ፡ በድል ፡ የተወጣበት ፡ ስያሳዊ ፡ መርሐ ፡ እና ፡ ስልት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ፍቱን ፡ ፈውስነቱንም ፡ በታሪክ ፡ ማስመስከሩን ፡ እናስታውሳለን ።

ሊ. ፡ **ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ** ፥ በ 1966–67 ፡ ዓ.ም. ፥ የወቷደራዊ ፡ ደርግን ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ከተቃወሙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋውያን ፡ ተወካዮች ፡ በተደጋጋሚ ፡ በተላከላቸው ፡ ውክልና ፡ እና ፡ ዐደራ ፡ መሠረት ፥ በስደት ፡ ዓለም ፡ ከጥቂት ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ **ኢ.ሀ.ሥ.አ.**ን ፡ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ በሐምሌ ፡ ወር ፡ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ ለንደን ፡ ላይ ፡ አቋቁመው ፥ ትግሉን ፡ በዚሁ ፡ ስልት ፡ መርተዋል ። እንሆ ፡ ዛሬ ፥ የ**ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፥ ይህኑ ፡ ሥራ ፡ በሰፊው ፡ በማረማመድ ፥ መላውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለማስተባበር ፡ ተነሥቷል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !

ሀገራዊ ፡ የአንድነት ፡ ሥልጣንኸ ፡ ከቀበሌ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ወረዳ ፣ እስከ ፡ አውራጃ ፣ እስከ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ እና ፡ እስከ ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚዋቀርበትን ፡ ትውፊታዊ ፡ ስልት ፡ በማዘመን ፥ ሀገራዊው ፡ የሥልጣን ፡ ተዋረድ ፡ የሚበጅበትንና ፡ ዐዲሱን ፡ ክዋኔኸን ፡ ( ወይም ፡ ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥትኸን ) ፡ በሕጋውያን ፡ ተወካዮችኸ ፡ አርቅቀኸ ፡ የምታጸድቅበትን ፡—

« ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ » ፥

እንሆ ፥ የኢ.ሀ.ሠ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ሲያሰናዳ ፡ ከርሞ ፥ የመጨረሻ ፡ ረቂቁን ፡ በዛሬው ፡ ዕለት ፥ መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ ያጸደቀው ፡ መኾኑን ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ያበሠርልኻል ።

ሰነዱንና ፡ ዐብረውት ፡ የሚወጡትን ፡ ተያያዥ ፡ ሰነዶች ፡ በቅርቡ ፡ በመርበቢያችን ፡ በ ፦

www.slttunhzb.net

አማካይነት ፡ ላስተያየትኽ ፡ የምናደርስልኽ ፡ መኾናችንን ፡ በታላቅ ፡ አክብሮት ፡ እናስታውቃለን ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

በሠልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽ ፡ ሙሉ ፡ ችሎት ፡ የማይፈታ ፡ አንድም ፡ ችግር ፡ የለብኽምና ፥ ዓመቱ ፡ ይህን ፡ ሀገራዊ ፡ ክሂልኽን ፡ የምታሞላበት ፣ ሀገራዊ ፡ እግዚአናኽን ፡ የምታስከብርበት ፡ እና ፡ ሠልጡንሕዝባዊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባዲስ ፡ ክዋኔ ፡ ( ባዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ) ፡ ዳግም ፡ የምትከውንበት ፡ ዓመት ፡ እንዲኾንልኽ ፡ **ኢ.ሀ.ሠ.አ.** ፡ ከልብ ፡ ይመኝልኻል ፤ በተጋድሎኽም ፡ ኹሉ ፡ ከጐንኽ ፡ አይለይም ፨

ትሑት ፡ አገልጋይኽ ፦

**ኢ.ሀ.ሠ.አ.**